# መግባባት በኢትዮጵያ የአጋርነት ጉባዔ
# መግለጫ

ጁን 30 ፥ 2018 እ.አ.አ - አሌግዛንድሪያ ፣ ቨርጂኒያ - ዩናይትድ ስቴትስ

በርካታ ኢትዮጵያውያን ባለፉት 50 ዓመታት በልዩ ልዩ የፓለቲካ እንቅስቃሴዎች ፣ ንቅናቄዎችና ድርጅቶች ውስጥ በመሳተፍ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ፣ ለህዝባዊ መንግስት መቋቋም ፣ ለብሔሮች መብት ፣ ለእምነት እኩልነት ፣ ሀሳብን ለመግለፅና ለፕሬስ ነፃነት ፣ ለማህበራዊ ፍትህ ፣ ለስርዓተ ፆታ እኩልነት ፣ ለመሬት ይዞታ ባለቤትነት እና ሌሎች መሰረታዊ ጉዳዮች ታግለዋል ፣ መስዋዕትነት ከፍለዋል።

በቅርብ ዓመታት በአዲሱ ትውልድ ሰፊ ተሳትፎ በተደረጉ ሰላማዊ ትግሎች ፥ በቀዳሚነት በ"ድምፃችን ይሰማ" ፅኑ የነውጥ አልባ ትግል አርዓያነትና ፋና ወጊነት ፣ ከዚያም በኦሮሚያ ክልል ተጀምሮ ፣ በአማራና በደቡብ ክልሎች ተቀጣጥሎ ሳያቋርጥ ለአመታት በርካቶች መስዋዕትነት የከፈሉለት ህዝባዊ ተቃውሞን ተከትሎ ከኢሕአዴግ ውስጥ ተራማጅ ኃይሎች ወደ ፌደራልና ክልል አመራር መጥተዋል።

ከህገራዊ ፓለቲካ አንፃር በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዓብይ አሕመድ አመራር ለረዥም ጊዜ ባልታዩ መልኩ በሀገራችን አዲስ የተስፋ ምዕራፍ ተከፍቷል። ይህ በሀገራችን የተፈጠረው በጎ የፓለቲካ መንፈስ ለሰላም ፣ ለዕርቅና ፣ ለተሻለ ሀገራዊ መግባባት ፣ ለሰብዓዊ መብቶች መበረታታት ፣ መከበርና ፣ መጠበቅ ፣ ለተሻለና ሚዛናዊ ፓለቲካዊ ሂደት መፈጠር ትልቅ ታሪካዊ አጋጣሚ ነው። አጋጣሚውን በጥንቃቄ፣ በኃላፊነትና በታታሪነት መጠቀም ከሁላችንም ይጠበቃል።

ቅዳሜ ጁን 30 2018 እ.አ.አ **በመግባባት በኢትዮጵያ የአጋርነት ጉባዔ** ዝግ የምክክር ስብሰባ ጊዜ በሰላም ፣ በዕርቅ ፣ በመግባባትና በሰብዓዊ መብት ላይ የሚያተኩሩ ድርጅቶች ፣ ስብስቦችና ግለሰቦች ፣ እንዲሁም የተጋበዙ የህግ ፣ የቅራኔ አፈታት ባለሙያዎችና መንፈሳዊ መሪዎች ተገኝተዋል።

በዚህ የምክክር ስብሰባ ላይ በሀገራችን የተፈጠረውን በጎ የፓለቲካ መንፈስ መርምረን ፣ በብዙዎቻችን ውስጥ የፈነጠቀውን የተሻለና ሚዛናዊ የፓለቲካ ሂደት የመፍጠር ተስፋ በዘላቂነት እውን ከማድረግ አንፃር ፥ የረዥም ጊዜ አቅጣጫን ፣ ወቅታዊ አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን ፣ እንዲሁም ያለፉ በደሎችንና ቁስሎችን በሚመለከት መክረናል።

ምክክራችን ወቅቱን ያገናዘቡና የሚመጥኑ ፤ የጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይን የመደመር ትርክት የሚያዳብሩና የሚገነቡ ፤ ህዝብን ከለውጥ መሰረትነት ባሻገር ንቁ ባለቤትና ተሳታፊ ማድረግ ይችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን 10 ነጥቦች አዘጋጅተናል።

እነዚህ አቅጣጫ ጠቋሚ ነጥቦች ፣ ዛሬ በሀገራችን በቅርበትና በንቃት የምንከታተለውን የተሻለና ሚዛናዊ የፓለቲካ ሂደት የመፍጠር ትልቅ ታሪካዊ አጋጣሚን አንድ እርምጃ ወደፊት ከማራመድ አንፃር በሚደረጉ ልዩ ልዩ ውይይቶችና እርምጃዎች ላይ እንደ አንድ ግብዓት የድርሻችንን ሚና ለመጫወት ከማሰብ ተነሳሺነት እንደሆነ በትህትና እየገለፅን ፤ ከሌሎች በሀገር ውስጥም ሆነ በዲያስፓራ ከሚንቀሳቀሱ ወገኖቻችን ጋር አብረን ለመስራትና ለመተባበር ዝግጁ መሆናችንን እናሳውቃለን።

1. **ሀገራዊና ሁሉን አሳታፊ ምክክር፦** በሀገራችን ባለፉት 27 ዓመታት ስኬቶች እንዳሉ ሁሉ ፣ ስጋቶችና አለመግባባቶችም ተበራክተዋል።

   *መሰረታዊና ዘለቄታዊ ሀገራዊ እንድምታ ያላቸው አለመግባባቶችን በሚመለከት ዛሬ የተፈጠረውን የተሻለና ሚዛናዊ ፓለቲካዊ ሂደት የመፍጠር ታሪካዊ አጋጣሚ በመጠቀም ሀገራዊ ምክክር የማድረግ አጋጣሚ ተፈጥሯል።*

   *መጪዎቹን ሁለት ዓመታት በአግባቡ በመጠቀም ፥ የሀገራዊ ምክክሩ ከቀጣዩ ሀገራዊ ምርጫ ጎን ለጎን ትኩረት እንዲሰጠው ጥሪ እናቀርባለን።*

2. **የለውጥ አራማጅ መሪዎችና የለውጥ ሂደቱ ደህንነት፦** ሰኔ 16 ፣ 2010 ዓ.ም. አዲስ አበባ በተደረገው የድጋፍ ሰልፍ ላይ የደረሰው የቦምብ ጥቃት በግልፅ  እንደሚያሳየው የለውጥ አራማጅ መሪዎች ደህንነት ልዩ ትኩረት ይገባዋል።

   ከዚህ አንፃር ሰፊው ሕዝብ የለውጥ አራማጅ መሪዎችን ደህንነት በንቃት እንዲጠብቅ ፤ እንዲሁም የመንግስት የደህንነት ፣ የፓሊስና የመከላከያ ተቋማት ከመቸውም በላይ በንቃት ስጋቶችን አስቀድመው የመከላከልና የመቆጣጠር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በትህትና እናሳስባለን።

3. **የለውጥ ሂደቱና የኢሕአዴግ አባላት፦** የለውጥ ሂደቱ የኢሕአዴግን አባላት ስጋት በሚያረጋጋ መልኩ በጥበብና በጥንቃቄ ሊቀጥል ይገባል።

   የኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎችም የኢሕአዴግ ሊቀመንበር ዶ/ር ዓብይ አህመድ ሚያሳዩትን ግሩምና ታሪካዊ አመራር በንቃት በመደገፍ የዚህ ታሪካዊ ለውጥ ተባባሪና አካል ሆነው እንዲቀጥሉ ጥሪ እናቀርባለን።

የለውጡ አራማጅ መሪዎችም ከህዝብ ያገኙትን ድጋፍ ዘለቄታዊነት ለማጠናከር እንዲቻል ፥ ሊነሱ ሚችሉ ክፍተቶችን አስቀድሞ የመቀነስና መቆጣጠርን አስፈላጊነት እናሳስባለን።

4. **ህብረተሰባዊ ፈውስ፦** በልዩ ልዩ ምክንያቶች በሀገር ውስጥና በዲያስፖራ የተጠራቀሙ ማህበረሰባዊ አለመግባባቶች ፣ ጥርጣሬዎች ፣ መራራቅና መቃቃሮች ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊነቱን ተረድተናል።

እንደ አቶ ለማ መገርሳ እና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ያሉ ፋና ወጊ መሪዎች የወሰዷቸው የመቀራረብና የመናበብ እርምጃዎችን የሚያንፀባርቅና የሚያስፋፋ ተመሳሳይ ስራ የተፎካካሪ ፓርቲ መሪዎች ፣

ምሁራን ፣ ባለሀብቶች ፣ መንፈሳዊ መሪዎች ፣ አክቲቪስቶች እና የሲቪክ ማህበራት መስራት ይጠበቅብናል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይን አርኣያነት በተግባር በመከተል ፥ መራራቅን በመቀራረብ ፣ ጥርጣሬን በመናበብ የማከምና የመፈወስ ስራን መተግበር የሁላችንም አስቸኳይ ድርሻ ነው። በተጨማሪም በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች የተፈናቀሉ ወገኖችን ወደ ቀድሞ ኑሯቸው የመመለስ ስራ ሊጠናከርና ሊቀጥል ይገባል።

5. ***ዲያስፓራው በተግባር ይደመር፦*** በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ዛሬ ከመቸውም በላይ ገንቢ ሚና የመጫወት አርኣያነት ይጠበቅብናል። መከፋፈልንና መራራቅን በመደመር ማሸነፍ የኛ ድርሻ ነው።

እንዲሁም ከዲያስፓራው ሀገራችን የምታድግበትን ሀሳብ ማፍለቅ ፣ ዕቅዶችን መንደፍ ፣ በተግባር ማዋል ይጠበቅብናል። ምሁራን እስከዛሬ የነበረውን ለየብቻ የሚደረጉ ሙከራዎችን በትብብርና በመደጋገፍ የፓሊሲ ተቋም ለመገንባት አቅምን በሚያጎለብት መንገድ ለጋራ ሀገራዊ ጥቅም እንትጋ።

የሀገራችንን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት መደገፍ ፤ በውጭ የተወለዱ ልጆቻችን ሀገር ውስጥ ህዝብን የሚያገለግሉባቸውን አጋጣሚዎች በመፍጠር ሀገራዊ ስሜታቸውን ማጠናከር ዲያስፓራው ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች ጥቂቶቹ ናቸው። ዲያስፓራው በተግባር ይደመር!

6. ***የመደመር ትርክት፦*** የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዓብይ የመደመር ትርክት ይበልጥ እንዲዳብርና እንዲገነባ በማድረግ ሊገጥሙ የሚችሉ የትርክት ጥቃቶችን አስቀድሞ በመከላከል ፡ የተሻለና ሚዛናዊ የፓለቲካ ሂደት የመፍጠር ታሪካዊ አጋጣሚውን ቀጣይነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

   ይሄንን ሂደት ዘለቄታዊ ከማድረግ አንፃር አማራጭ ፓሊሲዎችን የሚያቀርብ የፓሊሲ ልማት /policy development/ ተቋም ማደራጀት ወቅቱ ከሚጠይቃቸው ዋና ጉዳዮች እንዱ ነው። የፓሊሲ ጠበብት ፣ ዲፕሎማቶችና ባለሙያዎች በዚህ ሂደት ሰፊ ሚና መጫወት ይጠበቅብናል።

   ለወጣቶች የስራ ዕድል የመፍጠርን አንገብጋቢና አስቸኳይ ጉዳይ ልዩና አጣዳፊ ትኩረት በመስጠት የኢኮኖሚ ባለሙያዎች በጋራ እንዲመከሩበትና የፓሊሲ አማራጭ በአፋጣኝ እንዲያቀርቡ በትህትና እንጠይቃለን።

7. **የመብት ጥሰቶች፦** የሰብዓዊ መብቶችን እንዲያስከብሩ የሚጠበቁ የፍትህ ፣ የደህንነትና የመከላከያ ተቋማት በተቃራኒው የመብት ጥሰት መሳሪያዎች ሆነው ቆይተዋል።

   እነዚህ ተቋማት ወደ ተፈጠሩበት ዋና አላማ ፡ ማለትም የዜጎችን ሰብዓዊ መብት የማበረታታት /promote/ ፣ ማስከበር /respect/ እና የማስጠበቅ/protect/ ኃላፊነታቸው እንዲመለሱ በማድረግ በነዚህ ተቋማት ሲፈፀሙ የኖሩ ፣ ከትውልድ ትውልድ ያልተለወጡ ግፎች ፣ ሰቆቃዎችና ግድያዎች በምድራችን ላይ እንዳይደገሙ የማድረግ ዋስትና መፍጠር ትልቁ ወቅታዊ ኃላፊነታችን ነው።

   እነዚህን ተቋማት ከፓለቲካ ነፃና ገለልተኛ የማድረጉ ስራ ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎችና ሲቪክ ማህበራት ሰፊ ሚና እንዲጫወቱና መንግስትም እንዲተባበራቸው በትህትና እንጠይቃለን።

8. **ገለልተኛ ኮሚሽን፦** የመብት ጥሰቶችን በመረጃ ተመስርቶ ለመገምገም ፣ ለመገንዘብና ለመሰነድ እንዲያስችል ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን የማቋቋም አስፈላጊነትን እየተገነዘብን ፤ ይሄ ተቋም ለተጀመረው የለውጥ ሂደት እንቅፋት በማይፈጥር መልኩ እንዲንቀሳቀስ የማድረግን ኃላፊነት ተገንዝበናል።

   በተለይም በዚህ የለውጥ ወቅት ለቂምና ለበቀል በማይጋብዝ መልኩ ግፍና በደሎችን ለማስተናገድ ጥበብና ጥንቃቄ ስለሚሻ ፣ አያያዙ ላይ ጥንቄቃ በማድረግ አሁን ሊያስከትል ሚችለውን ያልተጠበቀ ውጤት ለመከላከል ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን እንዲቋቋም ጥሪ እናቀርባለን።

**9. የመብት ጥሰት ተጠቂዎች ድርሻ፦** የመብት ጥሰት ተጠቂዎች በተጀመረው የተሻለና ሚዛናዊ ፓለቲካ የመፍጠር ሂደት ሊጫወቱት የሚገባው ወሳኝ ሚናን ከግንዛቤ በማስገባት ፤ ተጠቂዎችን በለውጥ ሂደቱ ውስጥ ቀጥተኛ ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ በሀገራዊ ምክክር መድረኮች ላይ ሰፊና ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ወሳኝ ነው።

የመብት ጥሰት ተጠቂዎች በሰፊው መሳተፍ ከትውልድ ትውልድ የቀጠሉ የግፍና የስቃይ አዙሪቶችን በዘላቂነት ለማቋረጥ የሚረዱንን ተቋማዊ ለውጦችን ፤ እንዲሁም ለዘመናት የተሸረሸሩና የተጎዱ ግንኙነቶችን መልሶ ለመገንባት የሚያስቸውን የዕርቅና የማገገም ሂደት ለመጀመር ይረዳናል።

**10. ትምህርት፦** ዜጎች በዘላቂነት የተሻለና ሚዛናዊ የፓለቲካ ሂደት የመፍጠር ሂደቱ መሰረት ከመሆን ባሻገር ባለቤትና ጠባቂ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር ስለ ቅራኔ አፈታት ፣ ስለ ዕርቅ እርምጃዎች ፣ ስለሰላም ግንባታ ፣ ስለ

ሕገ-መንግስታዊ መብቶች እና የመራጭ ትምህርት /voter education/ በሚመለከት ማስተማር፣ ማንቃትና ማብቃት አስፈላጊነቱን እናምናለን። ከዚህ አንፃር መንግስት ፣ መገናኛ ብዙሃንና የሲቪክ ማህበራት ተጨማሪና ተገቢ ትኩረት እንዲሰጡ ጥሪ እናቀርባለን።

***መግባባት በኢትዮጵያ የአጋርነት ጉባዔ*** ከላይ የጠቀስናቸው 10 ነጥቦች ተፈትነው ፣ ዳብረውና ተስፋፍተው የተጀመረውን ፡ የተሻለና ሚዛናዊ ፓለቲካ የመፍጠር ሂደት በዘለቄታዊነት ለማስቀጠል ያግዛሉ ብለን እናምናለን።

በቀጣይነት በሀገር ውስጥ ካሉ ወገኖቻችን ጋር በጋራ "የመግባባት ጉባዔ" ለማድረግ ፈቃደኛ መሆናችንን በዚህ አጋጣሚ እንገልፃለን። በዚህ የጋራ የመግባባት ጉባዔ በፓሊሲ ላይ የሚያተኩሩ በሀገር ውስጥና በዲያስፓራ የሚገኙ ባለሙያዎችን ለማስተባበርና ለማቀራረብ ልዩ ትኩረት እንዲደረግ እንሰራለን።

ዘላለማዊ ክብር ዛሬ በሀገራችን የደረስንበት የተስፋ አጋጣሚ እንዲፈጠር የህይወት ፣ የአካል ፣ የሞራልና የቁሳዊ መስዋዕትነት በተለያዩ ዘመናት ለከፈሉ ወገኖቻችን ሁሉ ይሁን!

ኢትዮጵያውያን ለመግባባት የአንድነት መርበብ
Ethiopians for Consensus United Network

በቅዳሚው ዝግ ውይይቱ የተሳተፉ ድርጅቶችና ግለሰቦች፦

- *መግባባትን ገንቢ የኢትዮጵያውያን መድረክ*
- *ፎረም 65 / 65Percent.org*
- *የኢትዮጵያ የዕርቅና ርትዓዊ ፍትህ ምክር ቤት*
- *የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ፕሮጀክት (Ethiopian Human Rights Project)*
- *ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (Solidarity Movement for New Ethiopia)*
- *ያ ትውልድ*
- *CAHDE (Center for the Advancement of Human Rights and Democracy in Ethiopia)*
- *Peace and Justice in Africa*

- ***አቡነ ጴጥሮስ** - ከስደተኛው ሲኖዶስ የዕርቅና የሰላም አስተባባሪ*
- *ወ/ት ኤድና አለማየሁ - የሰላምና ቅራኔ አያያዝ ባለሙያ*
- *ዶ/ር ብርሃነመስቀል አበበ ሰኚ*
- *ዶ/ር መቅደስ ካሳ*